# National School Lunch Program 2023-2024 Letter to Households

Seattle Public Schools is committed to making its online information accessible and usable to all people, regardless of ability or technology. Meeting web accessibility guidelines and standards is an ongoing process that we are consistently working to improve.

While Seattle Public Schools endeavors to only post documents optimized for accessibility, due to the nature and complexity of some documents, an accessible version of the document may not be available. In these limited circumstances, the District will provide equally effective alternate access.

For questions and more information about this document, please contact the following:

Culinary Services
culinaryservices@seattleschools.org

# ብሔራዊ የትምህርት ቤት ምሳ ፕሮራም/ ብሔራዊ የትምህርት ቤት ቁርስ ፕሮግራም
# 2023–2024 ለቤተሰብ የተላከ መልእክት - የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች

የተከበራችሁ ወላጆች/አሳዳጊዎች፡
ይህ መልእክት ልጆቻችሁ ትምህርት ቤት እንዴት በነፃ ወይም የምግብ ዋጋ ቅናሽ ሊደረግላቸው እንደሚችል መረጃ እና ሌላ ተጨማሪ መረጃ ስለ ሌሎች እርዳታዎች (ቤነፊት) የሚሰጥ ነው። ትምህርት ቤቶች ስለ ሚያዘጋጁት ምግብ ዋጋ ዝርዝር ከዚህ በታች ይመልከቱ።
ቁርስ እና ምሳ **በነፃ ወይም የምግብ ዋጋ መጉደል እንዲደረግላቸ ኣመልክተው ለተቀበልናቸው** ተማሪዎች **በነፃ** ይሰጣል።
የተቀሩት ሌሎች ተማሪዎች በሚከተለው መሰረት ይከፍላሉ።

| የትምህርት ደረጃ | **መደበኛ ዋጋ** | | |
|---|---|---|---|
| | ቁርስ | ምሳ | መክሰስ (ስናክስ) |
| ኣንደኛ ደረጃ (ኤለመንታሪ) | $ 2.25 | $ 3.25 | የለም |
| መሃከለኛ ደረጃ | $ 2.50 | $ 3.50 | የለም |
| ሁለተኛ (ሃይ ስኩል) | $ 2.50 | $ 3.50 | የለም |

## ይህን የማመልከቻ ፎርም ማን መሙላት ይገባዋል?

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የምታሟሉ ከሆኑ ይህን ፎርም ይሙሉ:

- ዓመታዊ የቤተሰብ ገቢያችሁ እታች ሳጥኑ ውስጥ ከተዘረዘረው መጠን እኩም ወይም በታች ከሆነ፡
- ለልጆችዎ ቤዚክ ፉድ፣ ለኢንዲያን ረሰርቬሽንስ የሚደረግ የምግብ ማከፋፈል ፕሮግራም (FDPIR) ወይም ግዝያዊ እርዳታ ለተቸገሩ ቤተሰቦች (TANF) የሚቀበሉ ከሆኑ፡
- ለማደጎነት በሃላፊነት በሚያሳድግ ድርጅት ስር ወይም በፍ/ቤት ስር ለሚገኙ የማደጎ ልጆች የሚያመለክቱ ከሆነ
- ይህን የማመልከቻ ፎርም ምልተው ወደ የትምህርት ቤትዎ የምግብ አገልግሎት ያድርሱት ወይም በፖስታ ቤት በኩል በሚከተለው ኣድራሻ ወደኛ ይላኩት: Culinary Services - MS32-372; PO Box 34165 Seattle, WA 98124 ; ወይም ለምግብ አገልግሎት በፋክስ ቁጥር 206-252-0664 ይላኩ; ወይም በኢሜል culinaryservices@seattleschools.org ይላኩ::

ኣንድ የማመልከቻ ፎርም ለኣንድ ቤተሰብ መሙላታችሁን ኣረጋግጡ። ማመልከቻችሁን እንደተቀበልነው ወይም እንዳልተቀበልነው በጊዜ እናሳውቃቹሀ ኣለን። የሚያመለክቱለት ያሉት ልጅ የጎደና ተዳዳሪ ከሆነ (ማክኔይ-ቢንቶ) ወይም ስደተኛ ከሆነ የሚመለከትው ሳጥን ውስጥ ምልክት ያድርጉ።.

## የቤተሰብ ገቢ ምን ያጠቃልላል? ማን ነው ኣንድ ቤተሰብ ኣባል የሚቆጠረው?

እታች ያለውን የገቢ ቻርት ተመልከቱ። የቤተሰብዎን ቁጥር ያግኙ። ከቤተሰብዎ ቁጥር ጋር የሚስማማውን ጠቅላላ ገቢ ይመልከቱ። የቤተሰብዎ ኣባላት ደሞዝ በወሩ ውስጥ በተለያየ ግዜ የሚከፈሉ ከሆኑ እና ቤተሰብዎን ብቁ መሆኑ እና ኣለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ፤ ይህን ፎርም ዝም ብለው ይምሉት፣ እኛ በገቢዎ መሰረት ለዚህ እርዳት የሚበቁ እንደሆኑ እና እንዳልሆኑ እንወስናለን። ይህ የምትሰጡት መረጃ ልጆቻችሁ ለነፃ ወይም የዋጋ ቅናሽ የተደረገለት ምግብ ብቁ መሆናቸውን እና ኣለመሆናቸውን እንድንወስን ያግዘናል።

የማደጎ ልጆች በኣሳዳጊው ድርጅት ወይም ፍርድ ቤት ሃላፊነት ስር ሆነው ምንም ዓይነት የግል ገቢ ሳይታይ ለነጻ ምግብ ብቁ ይሆናሉ:: ስለ ለማደጎ ልጆች የሚሰጥ ነፃ ምግብ የሚመለከት ጥያቄ ካላዎ እባክዎ በሚከተለው የስልክ ቁጥር ደውለው ያነጋግሩን 206-252-0675

**የገቢ ቻርት**
**ከሓምሌ 1, 2023 እስከ ሰኔ 30, 2024 ተግባር ላይ የሚውል**

| የቤተሰብ ብዛት ሳምንት | በሳምንት | የዓመት | የወር | 2 x የወር | በ2 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | $ 26,973 | $ 2,248 | $ 1,124 | $ 1,038 | $ 519 |
| 2 | $ 36,482 | $ 3,041 | $ 1,521 | $ 1,404 | $ 702 |
| 3 | $ 45,991 | $ 3,833 | $ 1,917 | $ 1,769 | $ 885 |
| 4 | $ 55,500 | $ 4,625 | $ 2,313 | $ 2,135 | $ 1,068 |
| 5 | $ 65,009 | $ 5,418 | $ 2,709 | $ 2,501 | $ 1,251 |
| 6 | $ 74,518 | $ 6,210 | $ 3,105 | $ 2,867 | $ 1,434 |
| 7 | $ 84,027 | $ 7,003 | $ 3,502 | $ 3,232 | $ 1,616 |
| 8 | $ 93,536 | $ 7,795 | $ 3,898 | $ 3,598 | $ 1,799 |
| ሌላ ተጨማሪ የቤተሰብ ኣባል ካለ የሚከተለውን መጠን ለኣንድ ሰው ደምሩበት:: | +$ 9,509 | +$ 793 | +$ 397 | +$ 366 | +$ 183 |

**ቤተሰብ** ማለት እዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚከተለውን ይወክላል፤ ወላጆች፣ ልጆቻቸው፣ ኣያቶች እና ዘመድ ይሁኑ ኣይሁኑ እቤታችሁ የሚኖሩ ወይም ወጪዎቻችሁን የሚያከፍሉዋችሁ ያጠቃልላል። ማመልከቻችሁ ላይ የማደጎ ልጅ የሚያሳድ ቤተሰብ ብላችሁ እያመለከታችሁ ከሆነ፤ የማደጎ ልጅዎን ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት ውስጥ ሊያስገቡት ይችላሉ።

**የቤተሰብ ገቢ** ማለት ድምር ገቢ የሁሉም የቤተሰብ ኣባሎች ከታክስ በፊት ያጠቃልላል። ይህ ደሞዝ፣ ሶሻል ሴኩረቲ፣ ጡረታ፤ ኣንኢንፕሎይመንት፣ ዌልፌር፣ ለልጅ የሚሰጥ እርዳታ፣ በፍርድ ቤት የተወሰነ የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ እና ሌላ የሆነ ገቢ የገንዘብ ገቢ ያጠቃልላል። የማደጎ ልጅ እዚህ ማመልከቻ ውስጥ እንደ ቤተሰብ ኣባል ካስገባችሁት፤ የማደጎ ልጅዎን ገቢ የቤተሰብ ጠቅላላ ገቢ ውስጥ ያስገቡት። ለማደጎ ልጅ የሚሰጥ ልዩ ክፍያ ጠቅላላ ገቢ ውስጥ ሪፖርት ኣታድርጉት።

## ማመልከቻው ምን ማጠቃለል ይገባዋል?

**A. ምንም ኣይነት እርዳታ ለማያገኙ ቤተሰቦች:**

- የተማሪው ስም
- የሁሉም የቤተሰብ ኣባላት ስም
- የሁሉም የቤተሰብ ኣባላት ገቢ ከነምንጩ
- የቤተሰብ ኣስተዳዳሪ ፊርማ
- የሚፈርመው የቤተሰብ ኣስተዳዳሪ ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር የመጨረሻ 4 ቁጥሮች (ወይም "ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር የለኝም ካለ በሚመለከተው ሳጥን ውስጥ ምልክት ያድርጉ።)

ክፍል 1: 2 : 3 :4 እና 5 ይሙሉ::ክፍል 6 እና 7 ለመሙላት ግዳጅ የለብዎትም:

**C. የማደጎ ልጅ/ጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ብቻ:**

- የተማሪው ስም
- የቤተሰብ ኣስተዳዳሪ ፊርማ

ፎርሙ ውስጥ 1ደኛእና 5ተኛ ክፍሎች የግድ መሞላት ኣለባቸው። 6 እና 7 እንደ ምርጫችሁ ነው። ሌላ ኣማራጭ፤ ማመልከቻውን ከመሙላት ይልቅ፤ ልጁን እንድታሳድጉ የፈቀደላችሁን የፍርድ ቤት ውሳኔ ልትልኩልን ትችላላችሁ።

**ለ B የመጨረሻው 4 ዲጂት የሶሻል ሰኩሪቲ ቁጥር ኣያስፈልግም::**

| | |
|---|---|
| **B. <u>ቤዚክ ፉድ፣ ለኢንዲያን ረሰርቬሽንስ የሚደረግ የምግብ ማከፋፈል ፕሮግራም (FDPIR) ወይም ግዝያዊ እርዳታ ለተቸገሩ ቤተሰቦች (TANF) ለሚቀበሉ ቤተሰቦች</u>::**<br>• የሁሉንም ተማሪዎች ስም ጥቀስ<br>• የሰነዱን ቁጥር አስገባ<br>• የአባወራው ፊርማ<br>ክፍል 1: 2: 4 :እና 5 ይሞላ:: ክፍል 6 እና 7 ትን መሙላት የግድ አይደለም:: | **<u>D. የማደጎ ልጅ እና ሌሎች ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች</u>::**<br>እንደ ቤተሰብ ያመልክቱና የሚያሳድጉትን ልጅ ይጨምሩ:: የ A መመሪያ ይከተሉ:: ምንም እርዳታ የማያገኙ ቤተሰቦች እና የሚያሳድጉትን ልጅ የግል ገቢ ያካትቱ::<br>**ለ D የመጨረሻው 4 ዲጂት የሶሻል ሰኩሪቲ ቁጥር አያስፈልግም::** |

## ለቤዚክ ፉድ ገንዘብ እየተቀበልኩ ካልሆነ ማመልከት እችላለሁ?

ለቤዚክ ፉድ ኣመልክታችሁ ብቑ ሆናችው ሳለ ግን የቤዚክ ፉድ ገንዘብ የማትቀበሉ ከሆነ፤ ምናልባትም ለነጻ ወይም ለቅናሽ ክፍያ ምግብ ብቁ ሊሆን ይችሉ ይሆናል:: የግድ የምግብ ጥቅሙን ለማግኘት የምግብ ማመልከቻውን ፎርም በመሙላት ለልጅዎት ት/ቤት መመለስ አለብዎት::

## ኼዝ ነምበር ካላቸው ልጆቼ ያለ ምንም ነገር ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ?

ኣዎ። ግዝያዊ እርዳታ ለተቸገሩ ቤተሰቦች (TANF) ወይም ቤዚክ ፉድ የሚያገኙ ልጆች ይህን የማመልከቻ ፎርም ሳይሞሉ ነፃ ምግብ ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ ልጆች በትምህርት ቤት የመረጃ ማዛመጃ ዘዴ (ዳታ ማቺንግ) ሊታወቁ ይችላሉ። ይህ የተዛመደ ስም ዝርዝር ደግሞ ለልጅዎ ትምህርት ቤት የምግብ ዝግጅት ክፍል ይሰጣል። ይህ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ልጆች ደግሞ ትምህርት ቤታቸው የሚያቀርብ ከሆነ (ሁሉም ትምህርት ቤቶች የምግብ ኣገልግሎት ኣይሰጡም) ነፃ ወይም የዋጋ ቅናሽ የተደረገበት ቁርስ እና ምሳ ያገኛሉ። እባካችሁ ልጆቻችሁ ነፃ ምግብ እንዲያገኙ እንደምትፈልጉ እና እንደማትፈልጉ በተሎ ኣሳውቁን።

ልጆቻችሁ ይህን ዘዴ በመጠቀም ይህ የነፃ ምግብ ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፉ የማትፈልጉ ከሆናችሁ እባካችሁ ለልጃችሁ ትምህርት ቤት ኣሳውቁ።.

## ከቤተሰቦቼ ኣባላት ኣንዱ ኬዝ ነምበር ካለው፤ ሁሉም የተቀሩት ልጆቼ ለየነፃ ምግብ ፕሮግራም ብቁ ሊሆን ይችላሉ ወይ?

ኣዎ። ከቤተሰብዎ ኣባል ኣንዱ ኬዝ ነምበር ካለው፤ (ከማደጎ ልጅ በስተቀር) የግድ የነፃ ወይ ቅናሽ ምግብ ማመልከቻ ሞልታችሁ ወደ ልጆችዎ ትምህርት ቤት ሊልኩ የባል። በተጨማሪ የተቀሩ የቤተሰብ ኣባላት ልጆችዎ ይህን ነፃ ምግብ ሊወስዱ ይፈልጋሉ ኣይፈልጉም እባካችሁ በተሎ ኣሳውቁን።

## ቤዚክ ፉድ፤ ለምግብ ግዢ እርዳታ ብቁ ሊሆን እችላለሁ ወይ?

ቤዚክ ፉድ የመንግስት ፉድ ስታምፕ ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮግራም ለቤተሰቦች ወርሓዊ የምግብ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ የሚሰጥ እርዳታ ነው። ቤዚክ ፉድ ማግኘት ቀላል ነው! በኣካል ኣጠጋባችሁ የሚገኝ DSHS ጽሕፈት ቤት ኮሚኒቲ ሰርቪስ፣ በኢሜል ወይም በድሕረ ገጽ ልታመለክቱ ትችላላችሁ። ሌሎች እርዳታ የሚሰጡ ጽሕፈት ቤቶችም ኣሉ። ስለ ቤዚክ ፉድ 1-877-501-2233 በመደወል ወይም ለምግብ እርዳታ በድሕረ ገጽ http://www.foodhelp.wa.gov/basic_food.htm መረጃ ልታገኙ ትችላላችሁ።

## የሚሊታሪ ኣባላት ነን።. ለምግብ እርዳታ ገቢያችንን በተለየ መልኩ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅብናል?

የምታገኘው መደበኛ ገቢና ጉርሻ እንደገቢ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል:: በጥሬ ገንዘብ የሚገመት የቤት አበል: ለምግብ ወይም ለልብስ የሚሆን ሁሉ የግድ ገቢ ውስጥ ሊካተት ይገባል:: ይሁን እንጂ ቤትዎ የሚሊተሪ ቤት ከሆነ የቤትዎትን አበል በገቢ ውስጥ አያካትቱ:: ማንኛውም ለግዳጅ ስምሪት የሚከፈል ገንዘብ በገቢ ውስጥ አይካተትም ::

## የልጄ ማመልከቻ ባለፈው ዓመት ጸድቆ ነበር:: አዲስ ማመልከቻ መሙላት አለብኝ?

አዎን:: ማመልከቻዎት የሚያገለግለው ለዚያ የትምህርት ዓመትና ለአዲሱ ዓመት የተወሰኑ የመጀመሪያ ቀናት ብቻ ነው:: ት/ቤቱ ልጅዎት ብቁ መሆኑን ካልነገረዎት በስተቀር የግድ አዲስ ማመልከቻ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል::

## የተወሰኑ የቤተሰብ አባላት ሪፖርት የሚያደርጉት ገቢ የሌላቸው ከሆነስ?

የቤተሰብ አባላት እኛ በማመልከቻው ላይ ሪፖርት እንዲያደርጉ የምንጠይቆት አንዳንድ ገቢዎች ላይኖራቸው ውይም ጭራሹኑ ገቢ ላይኖራቸው ይችላል:: ይህ ሲሆን በተገቢው ቦታ ላይ 0 ይጻፉ:: ይሁን እንጂ ማንኛዉም የገቢ መጻፊያ ቦታ ባዶ ከተተወ ይህም እንደ ዜሮ ይቆጠራል:: እባክዎትን የገቢ መጻፊያውን ቦታ ባዶ ሲተው አዉቀው እንዳደረጉ ስለምናስብ ጥንቃቄ ያድርጉ::

## የጤና አገልግሎት ሽፋን

ስለ ለልጆች የሚሰጥ ጤና ኣገልግሎት ለመጠየቅ ወይም የበልጠ መረጃ ለማግኘት እባካችሁ የሚከተለውን ድሕረገጽ ጎብኙ http://www.wahealthplanfinder.org ወይም ወደ ዋሽንግተን ሂልዝ ፕላን ፋይንደር ብሰልክ ቁጥር 1-855-923-4633 ደውሉ።

## ልጄ ልዩ ምግብ የሚያስፈልጋት/ገው ከሆነ ማግኘት ይችላል?

ልጅዎ የተለየ ምግብ የሚያስፈልገው ከሆነ የት/ቤቱን ወይም የወረዳውን የምግብ አገልግሎት ቢሮ ያነጋግሩ

## የብቃት ማረጋገጫ (ፕሩፍ ኦፍ ኢሊጂቢሊቲ)

ይህ የምትሰጡን መረጃ እውነትነቱን ለማረጋገጥ በበኩላቸ ባልታሰበ ግዜ ሊመረመር ይችላል። ኣስፈላጊ ባልነው ግዜ ልጅዎ ለነፃ ወይም የምግብ ዋጋ ቅናሽ ብቁ ሰለመሆኑ ተጨማሪ መረጃ እንድትልኩ ልትጠየቁ ትችላላችሁ።

## ሚዛናዊ ፍርድ (ፌር ሂሪንግ)

# ብሔራዊ የትምህርት ቤት ምሳ ፕሮራም/ ብሔራዊ የትምህርት ቤት ቁርስ ፕሮግራም
# 2023–2024 ለቤተሰብ  የተላከ መልእክት  - የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች

የልጅዎን ብቁነት በተመለከት የወሰነው ውሳኔ ወይም የተጠቀምንበት የኣወሳሰን ዘዴ ካልተቀበሉት ወይም ገቢዎን ለማረጋገጥ የተጠቀምንበት መመዘኛ ካላረካዎ ወይም ካልተስማሙበት ፓቲ ዶርጋን የፌር ሂሪንግ ባለስልጣን ልታነጋግሯት ትችላላችሁ። ርትኣዊ ዳኝነት የማግኘት መብት ኣላችሁ። ስለዚህ ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ቤትዎ ዲትሪክት በስልክ ቁጥር 206-252-0675 በመደወል ቀጠሮ ማስያዝ ትችላላችሁ።

## ድጋሚ ማመልከት

በትምህርት ዓመቱ የጊዜ ክልል ውስጥ በሆነ ግዜ ለበኔፊት(ለነፃ ወይም የዋጋ ቅናሽ የተደረገለት ምግብ) ማመልከት ትችላላችሁ። የቤተሰብ ገቢ መጉደል ካጋጠማችሁ፣ የቤተሰብዎ ቁጥር ከጨመረ፣ ስራ ከቛረጡ ወይም  ቤዚክ ፉድ፣ ግዝያዊ እርዳታ ለተቸገሩ ቤተሰቦች (TANF) ወይም ምግብ የማከፋፈል ፕሮግራም ለኢንዲያን ረሰርቬሽንስ (FDPIR) መቀበል ከጀመራችሁ፤ ንቤኔፊቱ ብቁ ልትሆኑ ስለምትችሉ ማመልከቻ በፈለጉት ግዜ መላክ ይችላሉ።